**የጥናት ክፍል፡** ሐዋርያት 8፡26-39




**ርዕስ፡ ፊልጶስና ለኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ወንጌል ሰበከ**

በዚህ ታሪክ መሰረት ለአንድ ሰው ወደ ጌታ ለመምጣት 4 ዋና ወሳኝ ነገሮችን እንዳሉ እናያለን

1/ የመንፈስ ቅዱስ፣ 2/ የእግዚአብሔር ቃል እንዴት የአንድን ሰው ልብ የመንካትና የመለወጥ ሀይል እንዳለው 3/ የወንጌልን መልእክት ለማድረስ የሚታዘዙትን አገልጋዮች ፣ 4/ የአንድ ኃጢአተኛ ሰው ልብ ለወንጌል መታዘዝ እንዴት ወደ መዳን እነደሚያደርሰው፡፡

1. ክፍሉ ከተነበበ በኋላ ታሪኩን ስለምን እንደሚናገር ለቡድን አባላት ግለፁ (Head)

የመወያያ ጥያቄዎች

1. መላዕክት በወንጌል ሥርጭት ውስጥ ያለቸው/የነበራቸው ተሳትፎ ምን ይመስላል? (ዕብ 1፡14)
2. ጃንደረባ ማለት ምን ማለት ነው? (ማቴ 19፡12 1ቆሮ 7፡7-9)
3. የጃንደረባውን ማንነት ዘርዝሩ....
4. ፊልጶስ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ያነበው የነበረውን ክፍል ላይ በመመስረት ወንጌልን ለመስበክ እንዴት ቻለ? (ኢሳ 53፡5-8) አንተስ ሁል ጊዜ ስለ ጌታ ለመናገር ስትነሳ ወደ አእምሮህ ቶሎ የሚመጣው ጥቅስ ዬቱ ነው?
5. በማንበብና የምናነበውን በማስተዋል መካከል ያለው ልዩነት አብራራ
6. የዚህ ሰው ነፍስ ደንነትን ከኢየሩሳሌም (ቤተ መቅደስ) ሳይሆን በምደረበዳ ሆነለት ጌታን ያገኘህበትን የመጀመሪያ ቀን እንዴት ታስታውሳለህ፣ ዬትና እንዴት እንደሆነ መስከር፡፡
7. የውሃ ጥምቀት ላለመውሰድ የሚከለክል ምንድነው ?
8. የዉሃ ጥምቀት ወስደህ ከሆነ ያኔ የተሰማህን ደስታ እንዴት ታስታውሳለህ? ( ከሮሜ 6)
9. ዛሬ ወንጌልን ለመናገር ምን አይነት እድሎች አሉን?

II. ዛሬ ከክፍሉ እግዚአብሔር ለግልህ ያስተማረህ ምንድነው (Heart)
III. ዛሬ መንፈስ ቅዱስ ካስተማረን ውስጥ ልንተገብራቸው የሚገቡ ምን ምን ናቸው (Hand)